## ፫ ው ስ ጠ ወ ይ ራ ።

እንደ አንጻር ሁሉ ውስጠ ወይራንም ቅኔ የማያውቁ ሰዎች ከመምህራን ጠይቆ መረዳቱ ነውር ሁኖባቸውና ትዕቢት ተዘጥሮ ያደርጋል ደንቄሮ የሚለው ያባቶቻችን ተረት ደርሶባቸው በይመስላል የራሳቸውን ቅጀት እያወሩ ትውልዱን በፈጠራቸውና በልብ ወለዳቸው በከለው እንዳጠፉት ተረድተናል ፡ ብሎም ከዚህ የሚቀጥለው የአባ ቶቻችን ሕጋጌ የሥን ጽሑፍን ተከታታይ ሁሉ አዲስ ከሚፈጠረው ስሕተት ያድነዋል ብለን አምነን እውነተኛውን ውሳኔ በሚከተለው መሥመር እንጽፋለን ።

ውሳኔ ፡ የሰም ባለቤት ወይም ተሳቢ በወርቅ ዘርፍ ላይ ወድቆ ያልተጠራውን የወ ርቅን ኀዝ ሲያመጣ ውስጠ ወይራ ይባላል ። ውስጠ ወይራም የተባለው የወይራና የጨ ባ (ከውስጣቸው) የተለየ ሙርሙይ እንዳላቸው ይህም ከውስጡ የሚገኝ ነገር ስላለ በት ነው ።

ም.(ሀ) ገበሬ ጳውሎስ የክርስቶስን እኽል ዘሩ ፤ በሰምና በወርቅም ሕግ ሲፈታ የክርስቶ ስን እህል ሃይማኖት ዘሩ ፤ ያልተጠራው ሃይማኖት እንደ መጣ ያስተውሏል ።

(ለ) ኃይለ ሥላሴ የሰሎሞንን ልብስ ገዝቶ ለኢትዮጵያ ሸለማት ። ፍች ፡ የሰሎሞንን ልብስ ጥበብ ይላል ።

(ሐ) የፍቅርን ጠጅ የጠጣ ጐረምሳ ሰከረ

ሲዘረዘር የፍቅርን ጠጅ ትዝታ የጠጣ ጐረምሳ ሰከረ ።
ሲፈታ ፡ ሰም ጠጅ የጠጣ ጐረምሳ ሰከረ
ወርቅ ፡ የፍቅር ትዝታ ያደረበት ጐረምሳ ዛከረ ።
በግጥምም የሚከተለውን አብነት ያጠኗል ።
የባሕታዊ ልጅ ሲፈልግ ልዕልና
የክርስቶስን ምሽት ትላንት ወሸመና
ቅጠል ብታበላው ሁኖ ቀረ መና ።
ከባሕታዊ ልጅ ረኃብ ፡ ከክርስቶስ ሚስት ጾም ነው የሚወጣው
ከዚህ በላይ በተሰጠው ሕግ መሠረት በሚከተሉት ቅኔዎች
ውስጥ ያሉትን ውስጠ ወይራዎች እያወጣህ ጻፍ ።
የኢጣሊያን ወምበዴ እጁ የማያርፍ
ሀገሩን ሲገርፈው በሰማዕት ጅራፍ
ያገሬ ጐረምሳ በጣም ክልፍልፍ
የብረት አለንጋ ይዞ አለ ከተፍ
ሰነፉ ባንዳ ግን የፍርሃት እንጀራ
ያሚጥር ጀመረ ሆዱ ስለፈራ ።
ዝምድና ቢያጠና የምማር መስሎት
አበሻ ቄጠረ የአቤልን ልደት ።

የምትመገብ ሰው የስንፍና እንጀራ
አጥናው ተመልከተው ይህ ነው ውስጠ ወይራ
አንዘግዝገህ ጥለህ የራስህን ፈጠራ ፤

## ፮ ሰም ለበሰ ።

ስሙ እንደ ሚገልጠው ወርቁ በምሥጢር እንጂ ራሱ ሳይጠራ ሲቀር ሰም ለበሰ ይባላል ፤ ብዙ ጊዜ የሐልም ፍች ይመስላል ፤ ም. ዛፍ ትልቅ ሰው ፤ አባብ ጠላት ፤ እሳት በሽታ ፡ ወንዝ ዘመን ።

ኀይለኛ የዱር አንበሳ በተነሣ ጊዜ የግብጽ ላሞች ደነገጡ ። ሰምና ወርቅ ሲፈታ ሰም አይለውጥም ፡ ወርቅ ግን ማርቆስ ባስተማረ ጊዜ የግብጽ ላሞች ተዋረዱ ወዘተ የዚህ መጽሐፍ አንድ ሦስተኛው ሰም ለበስ ነው ። ራስዋ ሀገሪቱም በእናት የተመሰለችበት መንገድ በሰም ለበስነት ነው ። እያንዳንዱ ጠቅላይ ግዛት ኢትዮጵያ እስከ ምትመልስበት ድረስ ያለው ሁሉ ሰም ለበስ ነው ። በቤትም እንደ ሚከተለው ነው ፤

ትላንትና ማታ እጎረቤት ሂጄ
ክፉ ስለሰማሁ መጣሁ ተናድጄ
ያወሩ ነበሩ እናቴ ስላንቺ ፡
በቁመናሽ ሳለሽ እንዲሁ ሳትሞቺ ።
በካራ ዘልዝለው ጠብሰው በእሳት
ደግሞም እየቀዱ በብርሌ አሜት
ደምሽን ጠጥተው ሥጋሽን በሉት ።
እነሱ እንደሚሉት እውነት መሰለኝ
ነገር ግን እናቴ ስለሆንሽብኝ
ሐሜቱን ብሰማ በጣም ነደደኝ
ስለጠጉርሽ ብቻ እያንጐራጐሩ
ነገሩ ገርሟቸው ያወሩ ነበሩ ።
ባይጦቹ ከተማ በወፍ ሠራዊት
ዓለም ተሸበረ ሆነ ጦርነት
ወፎቹ ሲዋጉ በኀይል በጉልበት
አይጦች ተሰለፉ በረቂቅ ብልሐት
ዛሬ ሲያቸንፉ ነገ ሲቸነፉ
ይዋጉ ነበረ አንድም ቀን ሳያርፉ
ፍጥረት ሲተላለቅ መሬት ሲሆን ቁና
ጦርነቱ ሲቀልጥ ዓለም ሲባል ዲና
የሌት ወፍ ከዋሻ ተቀብራ በጤና
ይህን ሁሉ ትንግርት ስታይ ትውልና

ጦሩ ተመልሶ ሲረጋ አገር
ውጊያው ተፈጽሞ ሕዝቡ ሲገብር
ካሸናፊው ሰፈር ካሸናፊው ዱዳ
ጊዜያቱ ካለፈ ማታ ስትበር ሂዳ
ታወርደው ነበረ የዱራ ነገዳ ።
ገሥገሠ ወራት አለፈ ዘመን
ዓለም ሲተላለቅ በዚሁ አኳኋን
ኋላ ግን ደከመ የጦሩ እንፋሎት
የሠራዊቱ ኃይል የውጊያው ብርታት
ሲፋተግ ፡ ሲጋደል ሲታገል ሲላፋ
መመዛዘን እንጂ አሸናፊ ጠፋ ፤
ስለዚህ መከሩ ለመተራረቅ
ከመካከላቸው ጥፋት እንዲርቅ
ሽማግሌ ገባው ነገሩም በረደ
ዕርቃቸው በረታ ጠባቸው ወገደ
ፍቅራቸው ገነነ በጣም ፈደፈደ
ወፉን በወገኑ አይጡን በነገዱ
ሽማግሌዎቹ ሁሉን አሰናዱ
አማረ ሠመረ የዕርቁ ድርድር
ጠባቸው ሊጠፋ እንዲጠና ፍቅር።
ተራርቀው ሲያበቁ አንድ በግ ታረደና
ሥጋ እየጠበሱ ሲበሉ በደኅና
አንዱ ወገን መስሏት ያችው የሌት ወፍ
ምንም ሳታስተውል ብቅ አለች ካፋፍ ፤
ታክበው ሲበሉ ሁሉም ባንድ ቦታ
በሻጋሪ ሳለች ገና ሳትጠጋ ፡
ነዪ ተቀመጪ አሏት ከወፎቹ መንጋ
አይጦችም ተነሥተው ኖሪ ኀዴ አሏት
ገና ሳትጠጋ በሩቅ እንዳዩአት
ኀዴ ኀዴ ብለው ግራ ቀኛቸው
ዐይን ላይን ተያዩ ቅጡ ጠፍቷቸው
ሰው እንደ ተረዳው ይህን መጥፎ ሥራ
ወዲያው እንዳወቀች ጠፋች ከዚያ በራ ።
ሁሉም አሳደዷት ተገለጠ ገዷ
ከሁለቱ መካከል በመሰላወዷ

ሕሊናውን ቈርጦ ከልሠራ በግድ
ሁለት የወደደ አያገኝም አንድ ።

## ፺ ወርቃ ወርቅ ።

በጭሩ ነጠላ አንጻር ማላት ነው ፤ ወርቃ ወርቅ ሆኖ ግን ያለ እንደሆነ ጸያፍ ነው ማለት ይሆናል ። ጸያፍነቱም በአንድ ቀን ሁለት በዓላት ተደራርበው ሲውሉ አንዱን ሰም ሁለተኛውን ወርቅ ያደረገ እንደሆነ ነው ፤ ሚያዝያ ፳፯ ለት ነጻነታችን ወርቅ ስቅለት ንና ፀአተ ሲኦልን ሰም ያደረገ እንደሆነ ነው ። ወርቃ ወርቅና ነጠላ አንጻር አንድ መሆ ናቸውን ለመረዳት ከዚህ በታች የተጻፈውን ከነጠላ አንጻር ጋራ ያስተያዩአል ።

## ወርቃ ወርቅ ቅኔ ።

መጣ ገሥገሦ ያው ናፖልዮን
ከእስክንድር ጋራ መዝልጦ ሰይፉን
ጀግና ጓደኛውን ቴዎድሮስን
ከቤተ መንግሥቱ ድል አድራጊነት
በይፉ በገሃድ ሊሄድ ጕብኝቶት ።
የጦር ልብሱን ለብሶ ቴዎድሮስ ወጣ
ከሩቅ ለመቀበል ጓደኛው ሲመጣ ፤
ይዟቸው ገባና የሠራውን ቤት
በተራ ዐሳያቸው እንዲጕበኙት ።

## ፹ ልብሰ ወርቅ ።

ስሙ እንደ ሚያሳየው ወርቁ ብቻ ተጠርቶ በሰም ሲገሥ ልብሰ ወርቅ ይባላል ፤ በዚህም ጊዜ ወርቅ ሰምን ያመጣል ማለት ነው ። ሀ) ዝናማትን የፀነሱ ደመናት ነጐድ ጓድን ፈትለው መብረቅን ይለብሳሉ ። በሰምና ወርቅም ደምብ ሲገቡ እንደ ሚከተለው ነው ። ዝናማት ልጆችን የፀነሱ ሴቶች ደመናት ነጐድጓድ ጥጥን ፈትለው መብረቅ ልብስን ይለብሳሉ ።

(ለ) በጋ የሞተባት በለስ ቅጠሏን አወለቀች ፤
ፍች ፡ በጋ ባልዋ የሞተባት በለስ ሴት ቅጠል ጌጧን አወለቀች ።
ሰም ፡ ባልዋ የሞተባት ሴት ጌጧን አወለቀች ።
ወርቅ ፡ በለስ በጋ ቢያልፍባት ቅጠሏን አረገፈች ።
በግጥም እንዴት ያለ ውበት እንዳለው የሚከተለውን ይመለከቷል ፤
የወይኒቱ ታሪክ እንደ ሰማሁት
መስከረም ተፀንሳ ተወልዳ ጥቅምት
ታኅሣሥ የጥር ወንድም ለጋብቻ አጫት

ድግሱን ደገሱ ኅዳር የካቲት
ዳሯት አሳልፈው ሚያዝያ መጋቢት
ፍሬዋን ወለደች በወርኀ ግንቦት
አለፈ ጊዜዋ አርጅታ አፈጀች
በሰኔ ወር ታማ በሐምሌ ሞተች
ተገንዛ ታጥባ ከሣጥን ገባች
ነሐሴ አምስት ቀን አፈር ለበሰች ፣
ትነሣለች ብዬ አምናለሁ በእውነት
ኋላ በፍርድ ቀን በበጋ ምጽአት ።
ይህም ይቅርና የራምኖን ለት
በሰኔ ዘውድ ደፍቶ በኅዳር ሲሞት
ዓለሙ ሲያለቅስ እንዲያ ሲያዝንለት

## ፱ ቅጽል ተምሳሌ።

ሰም የወርቅን ዘርፍ ይዞ እንደ ባለቤት ሲመሰልና እንደ ዘርፍ አያያዥንቱም የቅጽልን ስሜት ሲሰጥ ቅጽል ተምሳሌ ይባላል ።

(ሀ) የሰሎሞን ልጅ ጥበብ ኃይለ ሥላሴን አገባች ። ከዚህ ልጅ የወርቅን ዘርፍ ሰሎሞንን ይዞ ከጥበብ ጋራ ተመስሎ የቅኔው ባለቤት እንደሆነ ያስተውሏል ።

(ለ) የፍቅር ጐረምሳ ትዝታ በአንጐል ኳስ ይጫወታል ፤ ፍቅር የወርቁ የትዝታ ዘርፍ ሲሆን ሰሙ ጐረምሳ እንደ ወደቀበት ይመለከቷል ።
ለግጥም የሚከተለውን አብነት ያነቧል ፤

(ሀ) ታላቁ ወጀብ የክረምት መስፍን
እያንቀጠቀጠ ሲገዛ ዓለሙን
ስታለቅስ ሀየኋት የበለስ እት ወይን

(ለ) ከዚህ ተቀምጬ ቁሚ ሳንጐራጉር
አለፈ ዘመኔ ጊዜያቱን ስቈጥር
ልውረድ አቈልቍዬ ወደ አገር መቃብር
አይወጣም ዕድሜ የማቱሳላ ደብር

(ሐ) አባያና ፈጣም ያባይ ገባሮች
አላሳልፍ አሉ መሰፍንት ሰዎች
ጠጥተው ጠጥተው ወተት ዝናምን
ሸፍተዋልና በክረምቱ ደን

(መ) ጌታው አቶ ስካር የባለጌ ዘውድ
ተገኘውን ሁሉ አደረገው እብድ ።

(ሠ) አ ሰው የዚህ ዓለም ባሪያ ፣

(ረ) ደግሞም በረኸኛ ፋሽሽት ገሎት ሊፈክር ሲሳሳ

ሰባብሮ ጣለው በበረሃ ጠቅል ዕንለ አንበሳ

## ፲ ዝ ም ድ ።

የተዛመደ ፡ ዘመድ የሆነ ማለት ነው ። ዘመድም የተባለበት ወርቅ ቀድሞ ሰም ተከ ትሎ ከወርቅ ዘርፍ ላይ ስለሚወድቅ ነው ። ለጀማሪ ከቅጽል ተምሳሌ ጋር ተመሳሳይ ይመስላል ግን ልዩ ነው ። ልዩነቱም ቅጽል ተምሳሌ የሚያሳየው ሰም የወርቅ ቅጽል መያዙን ብቻ ሲሆን ይህ ግን ወርቅ ቀድሞ ሰም ተከትሎ የወርቅን ዘርፍ መያዙን ጭ ምር ነው ። ለሁሉም ምሳሌውን ያጠኗል ።

(ሀ) ራምኖን የክረምት ልጅ ጠጉሯን ከፈከፈች

(ለ) ራምኖን የክረምት ቅቤ ፀሐይ ቢያየው ቀለጠ ።

(ሐ) ባለኜ የቈላ ፀሐይ ያቃጥላል ።

ሰምና ወርቅ ሲሆን ድርብ ውስጠ ወይራ ሲሆን ድርብ ይባላል ፤

ም. (ሀ) ቢታያት ዝናሙ ፤ የደመና ልጅ (ነጠላ ዝምድ)
ጠጕሯን አበጠረች ልምላሜ ወዳጅ ፡

(ለ) ትላንትና ነግሦ ያውም ባመሻሹ
ዝናም የደመና ንጉሡ ወራሹ (ድርብ ዝምድ)
መኳንንት መብርቅት ዋሉ ሲፈነሹ

(ሐ) ደጉ አቶ ብርሃኑ ያያ ፀሐይ ልጅ (ድርብ)
ይዞ ይመራዋል ዓለሙን ወዳጅ
ገደል እንዳይገባ ማስተዋሉን እጅ

## ፲፩ ፍ ላ ጻ ።

ፍላጻ የቀስት ጦር ነው ። የሰም ባለቤት ቀድሞ
ትንሹ ትልቁ ሲውል አፈር ለብሶ
ፊቱን አኰማትሮ እንደ ጠጣ ኮሶ

## ፲፪ መ ከ ዳ

ስሙ እንደ ሚገልጸው በፊትና በኋላ የውስጠ የና የግልጸ የ ቅጽል ሲኖረው መከዳ ይባላል ። ይኸውም ግራና ቀኝ ደገፋ ያለው ማለት ነው ። በግዕዝ ቅጽሎቹ ግራ ና ቀኝ ባለቤቱ ከመካከል መምጣት አለበት አማርኛ ግን በገባብ ልዩ ስለሆነ በዚህ አይ ገደድም ። የጊዮርጊስን አንገት የሳመች አፈ ክልፍልፍ ሴት ሰይፍ የቶማስን እጅ ጨበጠች ።

በግጥምም እንደ ሚከተለው ነው

(ሀ) የተቈረጠ እጁን ያ ቶማስ ቈማጣ
ጥሩ ፍትፍት ገድልን ሊፈተፍት መጣ ።

(ለ) የክርስቶስ አሽከር ሰማዕት ክልፍልፍ
ባንገቱ አነግቷል የተሳለ ሰይፍ

(ሐ) ያ ፈጣን ምላሱ የሚሮጥበት
ይዞት ገደል ገባ አድጦት ድንገት

(መ) በእንጀራ እናት በጋ እጅግ በሳሳች
ራምኖን ነዳ ጢሳ ነበረች
አሁን ግን ደስ አላት በክረምት ኰራች
ልምላሜ ተቀብታ አወለወለች ፡፡

(ሠ) የደም ገንበ ባትሽ የምትቆሚበት
አነሁሎ ፈጀው ያለሙን ፍጥረት

ከወርቅ ዘርፍ ላይ ከወደቀ በኋላ የወርቅ ባለቤት ስለሚከተለው ተወርዋሪ ለማለት ፍላጻ ተብሏል ፡፡ ለእሱም ነጠላና ድርብ አለው ፤ ዐዋጁም በአንጻርና በዝምድ እንደ ተናገርነው ሰምና ወርቅ ሲኖር ድርብ ሲጠፋ ግን ነጠላ ነው ፤ ም. የጳውሎስ እህል ስብ ከት ተበላ (ነጠላ ፍላጻ) የጳውሎስ ባለጸጋ እኽል ስብከት ተበላ (ድርብ) አብነት ፤

የክረምት ንጉሥ ዝናብ ልምላሜ መንግሥቱን ሲያሰፋ ዕራቁቷን ቀረች አሉኝ በለስ እንታችን ተዘርፋ ፡፡

### ፲፫ ሰም ገፊ፡

ከሁለቱ ስንኝ አንዱ ስለሰም ብቻ ሲያወጋ ዳግመኛው
ስለወርቅ የተረከ እንደሆነ ሰም ገፊ ይባላል ፡፡

(ሀ) ምን ቅጠል ናት ብዩ አሻግሬ ሳይ
ያች ሐረግ ሬሳ መሆንዋ ነው ወይ

(ለ) ጉብል ስታበጥር ዶሮ እየበላባት
እሽ ስትል ጊዜ እንዴት አማረባት ፡፡

(ሐ) ባቡር ገሠገሠ ገባ አሉ መተማ
ተብረከረክሁልሽ ድምጥሽን ብሰማ

(መ) ላሊበላ ሳሚ ላስታ መንገደኛ
ጫማ አድርጎ መሄድ መልካም አማርኛ ፡፡

ለዚህ መጽሐፍ መግቢያ ያህል ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የቅኔ ዐይነቶች ይበቃሉ፤ መወድሱን ግስ ለመረዳት ሰዋስው ግዕዛችን ማንበብ ያሻል ፡፡ የግጥም ተሰጥዎ ላላቸው ሁሉ ይህ መጽሐፍ ለቅኔ መግቢያ ይሆናቸዋል የሚል እምነታችንን ጥለንበታል ፡፡

### መ ቅ ድ ም ፡፡

በስመ አብ ልበልና ልጀምር ምስጋና፡
ለቅድስት ሀገሬ ሁኚ በትሕትና፡

እያልሁ ክብርት ነሽ ቅድስት ወብፅዕት
ያባቶቻችን የጀግኖች እናት
ለተክሊል አግብተሽ ንጉሠ ነገሥት
ሁነሽ ለምትኖሪው ዘለዓለም ቅድስት
ባለቅኔዎቹ ከኔ የተማሩ
ሌትና ቀን ብለው ሁል ጊዜ የሠሩ
መቸውንም አንድ አፍታ ምንም ሳያባሩ
ያላንዳች ውሳኔ ይዘርፉ ነበሩ
ለፋርስ ለባቢሎን ብበዙ ሲያወሩ
ለጽርዕ ለሜዶንም እንዲያ ሲናገሩ
በአእሮፕላን ዕውቀት ዓለሙን ሲዞሩ
መትረየስ ቅኔአቸውን ለሁሉ ሲዘሩ
ለናት ሀገራቸው ሳያቀምሷት ቀሩ
ይህ መደረጉ ስለምን ይሆን
ነግሠው መኖራቸው በአገር ቅኔያችን
የውጭ አገር ሰዎች ማይዘመዱን
ፋርስና ባቢሎን፣ ጽርና ሜዶን ?
እኔን የሚመስለኝ ላባቶቻችን
ሌላ አገር ያላዩ ያልገመቱትን
መስላ ታይታቸዋለች ጭቃና አፈርን
በመሃል እጅ ያለች ወርቅ ሀገራችን ።
ለዚህም ማስረጃ ወደ ሩቅ ሳንሄድ
መጥቀስ ያስፈልጋል አንድ ከሰው ልማድ
ሰው ሁሉ ይጓጓል ወርቅን ለመያዝ
በእጁ ከያዘው ግን ዕንቊም ሆነ አልማዝ
ሲቈጥረው ይኖራል እንደ አፈር ወርቁን
ብዙ ጉዳይ ሠርቶ ሚያስከብረውን ።
ይህ ደርሶባቸው ቅኔ እየዘረፉ
እሷን ሳያነሡ ብዙዎች አለፉ ።
ቅድስቷን ሀገሬን ላመስግን ማለቴ
በመብለጥ አይደለም እኔ ከነአባቴ
ያለፉትን ሁሉ በዚች አንደበቴ፤
አባቶቻችን ደክመው በትሕትና
ሰጡ ለሌላ አገር የኛውን ምስጋና
እነዚያ ሲገኙ በታላቅ ሙስና

እየመሰላቸው ያገኘን ልዕልና
ዛሬ ግን ተነሥቶ የቅናት ልቡና
ስሙን መለሰልን አመጣልን ዜና
ያባቶቻችንን የትሕትና ብዛት
ምስጋና ሲጽፉ ለባሕር ድመት
እያሉ ከሁሉ ዓይነ ብሩህ ናት
የኛይቱን ድመት ግን አይጡን በሌሊት
እያነቀች ስትፈጅ ያላንዳች መብራት
አገሬ በሆነች ድንፈፍ ናት አሏት
አንባቢ እናስተውል የዚህ በላዩን
ለሐሜት አይደለም የተጻፈልን
ለአብነት ነው እንጂ ለመጭው ዘመን
ወዲያ አርመን ጥለን ጉድለት አረምን
በአእምሮ ገምተን ሀገራችንን
ከሁሉ መብለጧን አንድነት ሁነን
እንድናፈቅር ነው ከልባችንን ።
አገራችን ሰትሆን ባለሙሉ ጸጋ
ለወይዘሮነቷ ሁልጊዜም ማትሠጋ
ዘለዓለም የማትወርድ ከነጻነት አልጋ ፤
የሷ ልጅ ተወልዶ በታላቁ ክብር
ለምርኮኛ ባሮች እንዴት ይገብር
በወርቅና በሰም ተሠርቶ ሲያምር
ላንቃ መወድስን ታላቁን ነገር ።
በዚህ በጠቀሰሁት በአሁኑ ነገሬ
ሚገባት ከሆነ ክብረት ለሀገሬ
ታጥቄ እጽፋለሁ እንግዲህ ዝማሬ።
እንደነ ተክሌና እንደነ ዕቡይ ካሣ (ቅኔ)
ፋርስና ባቢሎን ጽርን ሳላነሣ
በግጥም በቅኔ ላንሣት አገሬን
አቻ ባልንጀራ ማታገኘውን
ከመተንተን በፊት ቅጽና መልኳን
ደም ግባቷንና መልካም ውበቷን
መናገር ይገባል አቀማመጧን
ሐመር ሄሮዶቱስ እንደ ጻፋልን
ዐባይ ላባይ አርገው እንዳላፉ ግብጽን

ኤርትራንም አልፎ በአዶሊስ ወደብ
ሱዳንንና ኖባን አድርጋ ተዛኑብ
ቀኝዎቿ ሁነው በምሥራቅ እናረብ
የቀረው አፍሪቃ በምሥራቅ በደቡብ
ፍጥረት ሲሰግድላት እሷ ስታንጻብብ
በሌት ስታበራ እንደ አጥቢያ ኮከብ
ታንጸባርቅ ነበር ከሩቅ ላለ ሕዝብ
ትልቁ ወንበሯ ድሮ የነበረው
አሁን ከዚህ በላይ ባጭር የማልነው ነው
የድሮውን ቤቷን በትንሽ ካየን
ማድነቅ መገረሙን ለሌላ ትተን
በነቴዎድሮስ ስሙ ማይረሣ
በነ ዐፄ ዮሐንስ በነበዝብዝ ካሣ
በነዐፄ ምኒልክ በንጉሠ ኃይል
በግርማዊ ጃንሆይ በነአባ ጠቅል
በዚህ በአዲሱ አቅድ በአዲሱ ዘመን
በቄራጥ ሕሊና የሠሩላትን
እንሂድ እንድናይ አዲሱን ቤቷን
እሱንም ብናየው አቀማመጡን
ኤርትራን ሰፊ በር መተማን ተጋን
ኬንያን ደንበሩ ተዛንብ ሱማሌን
አድርጎ ይገኛል በአፍሪቃ ምሥራቅ
ሰፊው አደራሿ ጓኝው ዕፁብ ድንቅ
በጥበብ ተሠርቶ በብርና ወርቅ ።
ዓለሙን ሁልዞረን ደረስን ከቤቷ
ይሄው ገና በሩቅ ፈገግ አለ ፊቷ
በብሩህ ገጽና በጥሩ አንደበት
እንግዳን ስትመግብ ማርና ወተት
ለማስደሰት ብላ ሁሉን አንድነት
ሽማግሌ ሳትል ደግሞም ሕፃናት
ሄሮዶቱስ ሊቁ በሩቁ ያያት
ስላስደሰተቺው በብሩህ ልቡና
ሁሉን ስትቀበል ሆና በትሕትና
በዓለም እንዲታወቅ የምትሠራው ዜና
ደግሞም እንድታገኝ ከሁሉ ልዕልና

ታሪክ አስታቀፋት በሰፊ ምስጋና
ለእንግዳ ስትለግስ ልጆቹዋ የሆን
በልተን ምንሠራበት መች እናጣለን
ሀገር እናታችን ተቀምጣ ሳል
ልቤ ደረሰና ሰላም ለኪ ቢል
እጆቿን ዘርግታ በሕዝብ መሃል
ትዘምር ጀመረ እያለች እልል
መዝሙር አገባዳ ምክር ጀመረች
ከሁሉ አስቀድማ ልጇ ስማ አለች
ተግተህ እየሠራህ አመልህ ከቀና
እናትህ ሳለሁኝ በዚህ ዓለም ጤና
የሕግ ባሌ ንጉሥ ባለመልካም ዝና
ዕድሜው ከረዘመ ከኖረ በደኅና
ሠርተህ ምትበላበት ያውም በልዕልና
ስለማላሳጣህ እንዲያውም በጽሙና
ወዲያ አውልቀህ ጥለህ ብልኩን ብልግና
እንዳወጣ ሽጠህ ይህነን ስንፍና
በማለዳ ተነሥተህ ወዲያው ወደኔ ና
መቸም ያልታጠቀ ሰው አልወድምና፤

ልብ — በትሕትና ሆኜ እባክሽ እናቴ
ምስጋናዬን ላቀርብ በሙሉ አንጀቴ
ስለሚጣፍጠው ሶከሩ ፍቅርሽ
ለሰው አጥንት አርኪው መዓሩ ምክርሽ
ውዳሴ ወግናይ እያልሁኝ ዝማሬ
ላቀርብልሽ አሰብሁ ልጅሽ እኔ ዛሬ

ኢትዮጵያ — አልመካም እንጂ አምላክ በሠራኝ
በመልክና በደም ማን ሊታከለኝ

ልብ — እንዲህ ተደብቆ እንዳይቀር ውበትሽ
ፍቀጅልኝና ትንሽ ላሞግስሽ
ምንም ሐመር ባልሆን በግጥም ላይ እኔ
ደግሞ እንደ ተዋነይ ታላቅ ባለቅኔ
አንችም ብትበልጫቸው ወይዛዝርትን ሁሉ
ሐሳቤን ለመግለጥ ባልችልም በሙሉ
በያዝሁት ችሎታ እናቴ ነሽና
እባክሽ ፍቀጂ እንዳቀርብ ምስጋና

**ኢትዮጵያ** ውሰድ ፍጆታውን እኔ አጉራው ጠናኝ
በሚገባ አድርገህ እንድትጽፍልኝ

**ል ብ** ከሆነልኝ ለኔ ክቡር ፈቃድሽ
መወድስ ሣህልከ እንድቀኝልሽ
በቅኔ በግጥም እንዳወድስሽ
እንግዲህ ጀመርሁኝ ላመስግንሽ
ሕሊናዬ አዝማሪው መሰንቆ ሲመታ
አቀንቃኙ ልቤ ግጥሞችን ሲያንታታ
ውርዝዋን ዐይኖቼ ሲያቀልጡ ጭዋታ
ጆሮቼ ልሂቃን ሁነው በጸጥታ
ዘፈኑን ሲያደምጡ ከጠዋት እስከ ማታ
ሠርገኛው ሐሳቤ ዋለ በደስታ ፤
ከመግለጤ በፊት ቁንጅናሽንና ደግሞም ደም ግባትሽን
ልምላሜሽንና ያማረ ውበትሽን
እንዲያው ሳልቀባጥር በሙሉ መልክሽን
ላውጋቸው ለሰዎች አቀማመጥሽን
ከየት ባየናት ብለው የሚጓጉልሽን ፤
ዓለምን ደነቀው የቦታ ምርጫሽ
ፀሐይ እንዳይመታሽ ከደጋ ወጣሽ
የሰሐራ ሙቀት እንዳያከስልሽ
ተራራ ጃንጥላን ዘርግተሽ ይዘሽ
በቋንጢ ደጋሽ ላይ ካፋፍ ቀጭ ብለሽ
ደግሞም የደጋ ብርድ እዳይደርስብሽ
(ከንትሮስ) ምድጃን ካጠገብሽ አርገሽ
ቁርና አሳትያ ስለ ራቁልሽ
ከደስታ በቀር መከራ አያውቅሽ
አንች በደስታ ሁሉ ሞልቶልሽ
እንደዚህ ስትኖሪ በጣም ደስ ብሎሽ
ሱዳን ጎረቤትሽ ግብጽም ጓደኛሽ
በበረሃ ጥማት ሲጨነቁ አይተሽ
ዐባይ በሚባለው ትልቁ ጋንሽ
ጠጅ ውኃሽን ጥለሽ በተከዜ ዋንጫሽ
ሌት ተቀን ሳታርፊ ከዚያው እየቀዳሽ
በሰፊው ችሮታ ታጠጫችዋለሽ
እዩት የኔ ነገር አደረገኝ ወንጃ

ውበቷን ልናገር በብዙ ሳልጃጃ
ሳሰናዳ ሳለሁ ማልጄ አሳቤን
ሰፊው ችሮቷዋ ማረከው ልቤን
ማርኮትም አልቀረ መተማ ግብጽን
አድርሶ መለሰው በሕሊና ዓየር
ችሎቱን ሊያሳየው በሰማይ ሲበር
እለምናለሁኝ እመቤት ይቅርታ
ከፊትሽ ቁሜሳል አሁን በዚህ አፍታ
ለመልክ ለቁንጅናሽ ለማቅረብ ሰላምታ
በሥር ልጅሽ መጥቶ ሚባለው ችሮታ
ግብጽ ይዞኝ ወረደ ሁሉን ሊነግረኝ
መተማን ሱዳንን ሁሉን አዞረኝ
ፀሐዩ በርቶት ሙቀት ቢሰማኝ
ሩጬ ገብቼ እኔም ወዳንድ ቤት
ሰዎችን ብጠይቅ ሁሉም አንድነት
ዘርዝረው ነገሩኝ ችግራቸውን
በሕይወታቸው ሙሉ የሚገጥማቸውን
ደግሞም ገለጡልኝ ያላንዳች ሐፍረት
ምግብ ማድረጋቸውን ታላቁን ምጽዋት
የምትሰጺላቸውን አንች ዘለለት
ይህንን ሰምቼ በጣም ሲገርመኝ
ያንች ልጅ ችሮታ ይህን ነገረኝ
ኢትዮጵያ እናቴ እኔን ባትልከኝ
ዐባይን አሰይዛ ወደዚህ አገር
መተማና ሱዳን ደግሞም ይህ ስናር
እንደነ ሰሐራ ተቀበረው ከፈር
ይህን ጊዜ ትቢያ ይሆኑ ነበሮ
እያለ ሁሉንም ከልቡ እያወጋኝ
መልሶ ወደ አንች ደኅና ስላመጣኝ
ለጥ ብዬ እጅ ከነሣሁ ሥራዬን ቀጣይ ነኝ
የችሮታን ታሪክ ላልጨርስ አውግቼ
ውበትሽን ልግለጠው እሱን ለነገ ትቼ
ከላህይሽ በፊት ደግሞም ከውበት
እኔን የሚመስለኝ መቅደም ያለበት
ስለ መልክሽ ጥቂት ልናገር በፊት

ይዞ ስለሚገኝ የሠራ አካላት
ገተም ትልቅ ዕንጨት ዓለም ያወቀው
ንቧ የምትቀሥመው አበባው ማር ነው
እሼ ዋርካ ሾላ ፍሬያቸው ለምለም
ይህንን ከበላ ልጅ ምሳ አይልም
አጋምና ቀጋ ዋንዛና እንጆርይ
እግዚአብሔር ሰጥቶኛል ለልጄ ሲሳይ
ለንቋጣና ዶቅማ በበጋው ሲታይ
ብሉኝ ብሉኝ የሚል ይመስላል እንኮይ
በቅኔ በግጥም ደግሞም በዝማሬ
ስለመልክሽ ጥራት አወጋለሁ ዛሬ
ከመግባቴ በፊት ወደ ትንተናው
ልንገርሽ አድምጭን እንደምሠራው
ከግዕዝ የወለድሽው ልጅሽ አማርኛ
አባቱን ያከብራል ሁኖ በደንበኛ
አሁንም ይህን ዛሬ እኔ ስነግርሽ
ስለ መልክ ሳወራ ፊት እንዳይመስልሽ
ከራስሽ አንሥቶ እስከ ግር ጥፍርሽ
ሁሉም ሚነሣ ነው መላ አካላትሽ
አባቶቻችን ሁል ከዚህ ፊት የጻፉ
መልክም የደረሱ ሁሉን በየረድፉ
ከጓሌ አካላቶች አንዳችም ሳይረው
ይናገሩ ነበር ከግር እስከ ራሱ
እኔም እንደዚሁ በግዕዙ መሠረት
እጀምራለሁኝ መልክሽን ለማተት
ሰላም ልበልና ላንሣው አስቀድሜ
አቻ የሌለውን ጠጕርሽን ልምላሜ
ክረምትና በጋ አንድ ቀን ሳትረሽ
መጸውና ጸደይ ሳይለዩብሽ
ብትታይው ዓለም ያነን ከፍክፊሽ
ወደል ጋለሞታ ሐሳብ የሌለሽ
ልጅ ማታሳድጊ ትመሰዪዋለሽ
አንችና እኔ እናውጋ ተዩው ዓለሙን
ቀንቶብን ይሆናል የሚያሸሚጥጠን
ይድገመው ሐሜቱን ደግሞም ይሸርድዳን

የሚነሣን የለም እግዚአብሔር ከሰጠን
ይህነንም ስላልሁ አንድ ነገር አለኝ
ሁል ጊዜ በልቤ የሚያስጨንቀኝ
ብትወጅም ባትወጅም አሁን ከዚህ ቁሜ
እነግርሽአለሁኝ ኀዘኔን ተርጕሜ
በሆዴ አልይዘውም ፈርቼ ቅያሜ
አትበዪኝ እናቴ የዘመኑ ልጅ
ይሰድበኝ ጀመረ አድኅ ሳያፈጅ
እንኳንስ ይህነን ሌላውን ነገር
ላአንቺ ለመናገር እፈራ ነበር
ትላንትና ማታ እጐረቤት ሂጄ
ክፉ ስለ ሰማሁ መጣሁ ተናድጄ
ወጉን አሳጥሬ ልግለጥ ነገሩን
ከኒህ ከባዕድ ሰዎች የሰማሁትን
ያወሩ ነበረ እናቴ ስላንቺ
በቁምናሽ ሳለሽ እንዲሁ ሳትሞች
በካራ ዘልዝለው ጠብሰው በእሳት
ደግሞም እየቀዱ በብርሌ አሜት
ደምሽን ጠጥተው ሥጋሽን በሉት
እነሱ እንደሚሉት እውነት መሰለኝ
ነገር ግን እናቴ ስለሆንሽብኝ
ሐሜቱን ብሰማ በጣም ነደደኝ
ስለ ጠጕርሽ ብቻ እያንጐራጐሩ
ነገሩ ገርሟቸው ያወሩ ነበሩ
ምንም ልጅሽ ሁኜ ባልቀበለው
በልቡና ሚዛን ሳመዛዝነው
ሐሰትም አይደለ ነገሩ ዕውነት ነው ።
ከላይ ቅድም በፊት እንደ ነገርሁሽ
የሐሜቱ ሴማ ነበረ ጠጉርሽ
ዓለሙ ሁሉ ሲያልቅ ወዳጅ ዘመድሽ
ተላጭተሽ አታውቂም አንድ ቀን ብለሽ
በሰፊው ደግሳ ሕዝቡን አጠጥታ
በሚያስደንቅ ችሎት በአማረ ፈገግታ፤
ሁሉን ምታስከረው የበለስ አክስት
ወይዘሮ ወይኒቱ ለጋስዋ ብትሞት

በመከራው ጊዜ በጭንቁ ክረምት
ዓለም ሁሉ ሲያለቅስ ፊቱን እየነጨ
በልምላሜ ዐይኑ ላይ አፈር እየረጨ
በበረዶ ምላጭ እራስ እየላጨ
በሲቃ ወጀብ እየተበሳጨ
ረገዶን ሲያቀልጥ ነፋስ አቀንቃኝ
ኀዘን መንቀጥቀጥን ዓለሙ ሲቃኝ
መርዶውን ሲጮሁ በጆሮሽ ስምተሽ
ተኝተሽ ዋልሽ አሉ አንቺ ከቤትሽ ።
ይህም ይቅርና የራምኖን ለት
በሰኔ ዘውድ ደፍቶ በኅዳር ሲሞት
ዓለሙ ሲያለቅስ እንዲያ ሲያዝንለት
ትንሹ ትልቁ ሲውል አፈር ለብሶ
ፊቱን አኮማትሮ እንደ ጠጣ ኮሶ
አንች ግን ተኩለሽ ቅቤ ተቀብተሽ
ፊትሽን ወልውለሽ ጠጉርሽን ነቅሰሽ
በፍጹም የተዳረ ሙሽራ መስለሽ
የሁሉ ጌታ ሞት አይመጣ መስሎሽ
ወደ ልቅሶ ሳትሄጅ ቀረሽ ከቤትሽ
ይህነን ሰምቼ ሰዎቹ ሲያሙሽ
እየሮጥሁ መጣሁኝ እኔም ልነግርሽ
ኢትዮጵያ እኔ እንደ ሰማሁህ ያወራኸኝን
አድምጥ እስኪ ልጄ የምነግርህን
ልቡናህንና ከፍተህ ጆሮህን ።
ዘመድ ሞተ ብለው ፊታቸውን ሚፈጁ
ጠጉራቸውን ሚነጩ ያለቅጥ የጃጁ
አይደሉም የኔ አባት የክርስቶስ ልጁ
ለወንጌል አሽከርም ለጳውሊ ወዳጁ
አሽከር ናቸው እንጂ የከንቱ ዓለም
በቅጽበት የሚያልፈው እንደ ሕፃን ሕልም
እረ እነማናቸው አልቅሰው አዝነው
መልሰው ያመጡ የሞተውን ሰው
እኔስ አላለቅስም ነግሮኛል አባቴ ስሙ ክርስቶስ
ደክሞም የሱ አርበኛ ቅዱስ ጳውሎስ
እረ ለምን ብዬ እናትህ ላልቅስ

ስሕተት አይደለም ወይ ብታየው አንተስ ?
በደል እንደሆነ በጣም ሚያስደንቅ
ሰምቻለሁ እኔ ከተማሪ ሊቅ
ያውም ከዮሐንስ ቅጽሉ አፈ ወርቅ
ዘመድ ሞተ ብሎ የሚያለቅስ ሰው
ትንሣኤን የማያምን አረመኔ ነው ።
ልብ እውነትሽ እናቴ እንደ ቅዱስ መጻፍ
ማልቀስ አይገባም በከንቱ መለፍለፍ ።
ነገር ግን ሚደንቀው በሙሉ ዓለሙን
በወዳጅሽ ልቅሶ በወይዘሮ ወይን ፤
ኤውሮጳ በሞላ ሲፈጁ ፊታቸውን
እስያ ካናዳ ሲነጩ ጠጉራቸውን
ሲገርፉ አካላቸውን በቀጋ በረዶ
ደሙ እስኪ ወርድበት ሥጋቸው ተጎርዶ ፤
ግብጽና ሱዳንም ያንች ጐረቤት
እንዲያ አመድ ሲለብሱ በራምኖን ሞት
አንች ግን ይህን ሁሉ እንዳልሰማሽ ሁላ
ቁጭ ብለሽ በወንበር ከዛፎችሽ ጥላ
በልተሽ ስትስለች የማሩን ወለላ
ትፈለፍዪ ነበር ከወይኑ ዘለላ
እናቴ ከሆነ እንዲህ ልማድሽ
በምን ይታወቃል መውደድ መጥላትሽ
ደግሞም ይህ ከሆነ አቅዱ ለኑሮሽ
በጋ ክረምት ሳትዪ ባለው ዘመንሽ
አንድ ጊዜ ሳታዝኚ ዘለዓለም ስቀሽ
ኀዝንሽ መቼ ነው ደግሞስ ደስታሽ
ጥያቄውን ሁሉ ከዚህ ላይ አቁሚ
ዙሬ ልመልከተው ጠጉርሽን ልምላሜ
ዐይተው የጠንቡት በአገት የሰከሩ
መቼም አይገኙ ዓለሙን ቢዞሩ ።
ተላጭተሽ አንድ ጊዜ አላየሁ ቀምቀሞ
ዘለዓለም ይኖራስ ልቤ እንዲህ ተገርሞ
ይመክሩን ነበረ አባቶቻችን
በሰኔ እንድንላጭ የራስ ጠጉራችን ፤
አንች ግን ትተሽው ሁሉንም ንቀሽ

ወጠብሽም አየውቅ ምላጭ ከራስሽ
ሴት ናት ብዬ ላውራ ወይስ ቆንጆ ነሽ
እንደፊቱ እንዳልል ፡ ወግ እንዳልደረስሽ እንዳላገባሽ
በጋ ክርምት ሳትዪ ነጭ ልብስ ለብሰሽ
ሁል ጊዜ ዘለዓለም መቸም ሳይከፋሽ
መልካም ቆንጆ መሰልሽ በፓሪስ ያለሽ
ለጥቢ ሽርሽር ለቱሩ ብለሽ
የደናግሉን ጌጥ አበባ አደርገሽ
የሚያዩሽን ሁሉ ልብ እየማረክሽ
በዱሩ መንገድሽ ትፋስሻለሽ
ሁለተኛውንም እኔ እንዳላወራ
ቆንጆ ናት እያልሁኝ ጠቢያችን ሙሽራ
ወልደሻል ልጆችን ግርማቸው ሚያስፈራ
መልካቸው ሚያስደስት ሙያቸው ሚያኰራ
እኔ አይቼ አላውቅም እንዲህ ያለ ሥራ
በሁለቱም ቢያስቡት የሚያገባ ግራ
እንዲህ ያለ ነገር ሰሚን ይገርማል
እናቴ ቆንጆ ናት አሁን እኔ ብል
ሰው ይለኛል እንጂ ይኸው መጣ ቂል
እውነቱን ነው ብሎ አሁን ማን ያምናል
ድንግል ወእም ሁና የተገኘች በዓለም
ያለ ቅድስት ማርያም ሌላ ሴት የለችም
እያሉ ሲሰብኩ አበው ሊቃውንት
ይችውነን አንች ድንግልና እናት
ተገኘሽባቸው እንዲያው በድንገት
በደኅና እያለነ እኛ ልጆችሽ
ደግ እናትነትሽን ማን ነው ሚከዳሽ
ለድንግልናሽም አበባው አለሽ
የምታጌጭበት ሁል ጊዜ አድርገሽ
እንግዲህ ስለዚህ እኔ አልናገርም
እኩሉ ሲደነቅ እኩሉ ሲገረም
እያመነ ሲሄድ አይቶ የተረዳው
አዲሱ ሲመጣ ያላየ ያልሰማው
ለዚያ ማስረዳቱ ልቤን አዳከመው
ስለዚህ መናገር ጭዋታ ነው ከንቱ

ያልሰማ ላያምን ከኔ በመስማቱ
ሌላውም ይረዳል ቅሉ በማየቱ
ልምላሜው ጐፈሬሽ ሕዝቡን አስጨነቀ
ዕፁብ ድንቅ እያለ ያየሽ ተደነቀ
እስከ ዚህ ይብቃና ስለጐፈሬሽ
እንጀምር ፍቀጂ እናት እባክሽ
ጥቂት ለመናገር ስለ አካላትሽ

## ምዕራፍ ፩፡

አገር ተደነቀ በልምላሜሽ ጋሜ
ደሞም ሲነሆልል እኔ ዐየሁት ቁሜ
በሄትም አይገኝ ያልተመኘ ሰው
እያለ በልቡ ምነው ባገኘው
ዓለሙን ማረከው አውራሪው ጋሜሽ
ከመድረሱ በፊት ደጀኑ ፊትሽ
አካላትሽን ሁሉ ባጭር ባጭር ፍች
በጣም እንደትኰሪ ልንገር ለሰዎች
ጋሜሽን ከነገርሁ ከብዙ በአጭሩ
ልቁጥር አካላሕሽን ደግሞ እንደ ነገሩ ።
ከመጀመር በፊት አካልሽን ለመቁጠር
ለአዲስ አበባችን ራሽን ልናገር ።

## አ ዲ ስ  አ በ ባ ። (ራ ስ)

ራስሽ ተቀብቶ ቢታይ ቅብዐ መንግሥት
ዓለም ሁሉ መጣ ከሩቅ ሊሰግድለት ።
በትክለ መልካሙ አዲስ ራስሽ
በጣም የሚያስደንቅ ዘውድሽን ደፍተሽ
ቍጭ ብትዪ ጊዜ በወርቅ ዙፋንሽ
በመላ አከላትሽ ተደስተልሽ ።
ጰጳሳት ጊዮርጊስ እንጦጦ ማርያም
መንበረ ጸባዖት ታዕካ ነገሥትም
ካባ ላንቃ ለብሰው በጣም ሚያስገርም
እሱ መድኀኔ ዓለም እየረዳቸው
ጸሎቱን ሊያደርሱ ከልብ አስበው
ይደግሙ ጀመረ ሥርዓተ ንግሡን

ባርከው ሊያቀብሉሽ ዘውድና ሉሉን
ካህናት በሙሉ ጴጥሮስ ጳውሎስ
ደብትር ዲያቆናት እነስጢፋኖስ
ያገለግላሉ በሥርዓተ ንግሥ ።
ቅስና ዲቁና ሊቀበል ዓለም
ጳጳሱ ካሉበት ቅድስት ማርያም
ራስሽን ያየ የማይደርስ የለም
መላእክተ ሰማይ ገብርኤል ሚካኤል
ዐቢይ ራጉኤል አፍኒን ዑራኤል
ሩፋኤል መልአክ ሰው ሚያገለግል
ዘውድሽን ሊያከብሩ ሊሰሙ ጸሎት
በመላ ተገኙ ሐራ ሰማያት
መላእክት ሰማዕታት የጦር ሠራዊት
ለዘውድሽ ሲነሩ ቀርነ መለከት
እምቢልታ ጥሩንባ ደባይ ነጋሪት
መሰንቆና ክራር ልዩ ልዩ ዐይነት
የሰውን አእምሮ በጣም ሚያስደስት
በየግንቡ ሁነው ተግተው ሲዘምሩ
ስለራስሽ ውበት ያወሩ ነበሩ ።
ዓለም ተደነቀ ተገረመ ሰው
ከሰው ልጆች ጋራ አንድነት ሁነው
መላእክት ቢያደንቁ ራስሽን ዐይተው ።
አዲስ አበባ ራስ በጣም እንዲከበር
ደግሞም እንደታየው ከሩቅ ላለው ሀገር
ጥበቡ የማያልቅ ደጉ ምኒልክ
ፍጥረት ሁሉ እንዲለው ዘዓለም ቡሩክ
ከአቃቂ አንገት ከንጦጦ ጠጉር
ከፊተኛው በላይ ከኋለኛው ሥር
አድርጎ ተከለው በታላቅ ምሥጢር
ከዕለታት አንድ ቀን ሄጄ ወደ እንጦጦ
አቆልቁዬ በየው ሁሉ ተገልብጦ
ከተማው ቢታየኝ አንድም ሳይቀረኝ
እገጥም ጀመረ እንዲህ እያለሁኝ
ስምን ያወጣዋል መላኩ ብለው
ይጠቅሱ ነበረ የቀደሙ አበው ፤

ደግሞም ይሉ ነበር የሁሉን ዕድል
ከአርባ ቀን ጀምሮ ስም ይመራዋል
ግንቦችን ለማየት ዓይኔ ሳይሰለች
አዕዋፈ ሰማያት አዕሮፕላኖች
ይንጃብቡ ጀመር በአዲስ ሰማይ
ሕዝቡ ሁል አንጋጦ ሰማይ ሰማይ ሲያይ
እኔን የገረመኝ ልቤን የደነቀው
የራእየ ዮሐንስ ፍጻሜ መድረስ ነው ።
ብሎ ጽፎ ነበር ሰዎች በትውልድ
እግራቸው ይጮኻል እንደ ነጐድጓድ ።
እግር የተባለ ይህ መኪናቸው
ገና በሩቅ ሲሄድ ያሰፈራል ግርማው
ሰዎቹ በረሩ በምድር ሠረገላ
በሰማይም ሄዱ እንደ ምድር ሁላ ፤
ትጋት የሠራለት ልብስ ባሕር ዛፉን
ሐሩር እንዳይመታው ቀን ፀሐይ ሲሆን
ደግሞም እንዳይበርደው ብርዱ ሌሊቱን
ዘርግቶ ይውላል ቀን እንደ ጃንጥላ
ደግሞም ተጐናጽፎት ሌሊቱን በሞላ
አዲስ ራሳችን በጣም ሀብታም ነው
ባሕር ዛፍ እስካለ ችግርም የለው
የአዲስ ራሳችን ሀብቶቹን ልቁጠር
በሰው ሁሉ ዘንዳ ሚሰጡትን ክብር ፤
በአባ ጠቅል ኃይሌ እንጅነሪው ኃይል
ብዙ ቤቶችና መንገዶች ሠርቷል
ለእንግዳ ማደሪያ እነራስ ሆቶል
ለሕዝብ የሚጠቅም በሰፊ አቁሟል
ለደዌ ማገጃ ለትሎችም መግቻ
አሉት ሆስፒታሎች የነደጃች ባልቻ
እንደነ ምኒልክ እንደነ ራስ ደስታ
ለሕሙማን ሁሉ የሚሰጥ ጸጥታ
ደግሞም ሆስፒታሉ ለኃይለ ሥላሴ
ሕይወትን ሰጠልኝ ለሥጋና ነፍሴ ፤
ደዌ ተፈጠመ ወጥቶ አደባባይ
በኃይለ ሥላሴ በልዕልት ጸሐይ

ልዕልት ዘነበ ወርቅ ብትሠራ ለጤና
ሀገር በለጸገ ጠፋልን ቊምጥና
እመን በማኑኤል ጓዴ አትጠርጥረው
እንኳንስ ሌላውን ዕብዱን አዳነው
እንደ ጌታው ሁላ ቅዱስ ጳውሎስ
አይጠይቅም ዋጋ ሕሙም ሲፈወስ
አሁን በየት አለ እንዲህ ያለ መምህር
ዋጋ ስጡኝ ሳይል ድኆችን ሚያስተምር
የጥንቱ ንጉሥ የበረሃው ዳኛ
የሀሬ መኮሪያ የጠላት ደመኛ
ጦር የማይበግረው ችግር የማይፈታው
የጠላት ደም ጠጁ ጥይት እንጀራው
ያበሻ ወታደር በጣሙን ጀግናው
ተዋግቶም ቢቆስል እየሠራ ጀብዱ
ዋዕዩ ሲያቃጥለው ሲያራግበው ብርዱ
የሕመም አደጋ ቢያገኘው ድንገት
ዕለቱን ይድናል በጦር ሐኪም ቤት
ቁስሎ ለመታከም ከዚሁ ሲደርስ
የሕንፃው ዕዳቱ ይሰጠዋል ፈውስ
ይህን ያየ ወቴ ኵሩው ዘለዓለም
ሞትንም አይፈራ እንኳንስ ሕማም
ያ ደዌ ጠላቴ ወታደር ይላል
የተዋበችቱን ሀገሬን አካል
የምድር ጦር ሳለ መች ይደፍራታል
ሕዝቡን ሲያስጨንቀው በሽታ ባላንጣ
የምድርን ጦር አይቶ ጥሎ ፈረጠጣ!
ባበባው በግንቡ በተክሉ ለምለም
ለሚዘዋወር ሰው ሲያገኘው ድካም
እንኳንስ በሽታ ሞት ያለ አይመስልም
የክቡር ዘበኛ መኳንንቱ ሐኪም
ድውይ ለመፈወስ አቻ የለውም
እነሱ መንግሥቱን ሐኪም እነሱን
ይጠባበቃሉ ተግተው ሌት ተቀን
የሚያንፀበትም አንጐል ማኀደርን
በብዙ አሠርቷል ትምህርት ቤቶችን

ብረት ድንቍርና እንዳይቀር ተከብሮ
መዶሾችን ትምህርት አጠፋው ሰባብሮ
ስንፍና ብልግና በወረራ ገብተው
እንዳይቀሩ ብሎ አገራችን ገዝተው
ብዙ ቤተ ትምህርት ወታደር አበጀ
በመጽሐፍ መሣሪያ በጣም የደረጀ
ወደ ፊት መራመድ መሥልጠን ግንቡን
በምኒልክ ዘመን የጀመረውን
በኃይለ ሥላሴ ፈጸመው አሁን
ያዲስ አበባን ሀብት በመላ ለመቁጥር
አለመቻላችነን ማንም አይጠረጥር
እንቈጥራለን ብለን በመላ ሳይሆን
በትንሹ እንቍጠር የተቻለንን
በፊት ትምህርት ቤቱን የሚያኰራንን
ቀደም ተከተሉን በተራ ይዘን ።
አዲስ ትምህርት ቤትን የቈረቈረው
ምኒልክ ነው አሉ እግዜር ያላቀው
ከሁሉም ምኒልክ ዕድለኛ ሰው
ጣልያን ድንቁርናን አመድ አበላው
ተፈሪ መኰንን መልካሙ ጉልማሳ
እሱን ተከተለው በጣም እያገሳ
ጕልማሳ እንዲሆን ያውም ኃይል ያለው
ከኃጢአት ስንፍና ሙቶ ያዳነው
አምላከ ብርሃን መድኅኔ ዓለም ነው
እንረዳዋለን በሥራው በገብሩ
እሱን ተከትለው ሕፃናት ሲማሩ
አርበኞች ባላባት በጣሙን የተጉ
ጣላት ድንቍርናን ጠንክረው ተዋጉ
መጽሐፍ ብታሳየወ እቴጌ መነን
ስንፍና ብለግና የሴቶች ጋኔን
ጥሏቸው በረረ በጥቂት ዘመን ።
ምሱ እደ ጥበብን በልቶ ምሎ ሄደ
ዳግመኛ እንዳይመጣ በጣም እየራደ
በስም አብ ወወልድ ብሎ በቅድስት ሥላሴ
ቢያጠና ተማሪ ይቀጠቅጥ ከይሴ

ይህነን ቢሰሙ ትዕቢት ድንቍርና
ጠርተው ቢጤያቸውን ስንፍና ብልግና
በረው ገደል ገቡ ሁነው ቀሩ መና ።
ሀኬት ክፉ ሰይጣን በቅድስት ሥላሴ
እሰይ ተቸነፈ ደስ ይበልሽ ነፍሴ ።
በኃይለ ሥለሴ በአንደኛው ደረጃ
ስንፍና ቈሰለ መዳኑንም እንጃ
ካሣ የነፍስ ዋጋ ደግሞ እንዳይፈልግ
አቍሳይ የንጉሥ አሽከር አወይ ምን ያድርግ
የመሳፍንት ልጆች የሚማሩበቱ
ሰው ያነሆልላል የናዝሬት ጽዳቱ
በናዝሬት ተወልዶ ፈጣሪ ትምህርት
ለዓለም ሁሉ ሆነው ዕውቀት መድኃኒት
ሁሉን አስተማረ በናዝሬት ተዛውሮ
ሰውን ማክበርና ምግባርም ጨምሮ
ስንፍና እንዳይገባ በኀይል በጉልበት
ኮተቤና ወንጌት በሩን ያዙበት
ተግተው እያጠኑ መጽሐፍ ቢያሳዩት
ሀገር ለቆ ጠፋ የሰው ልጅ ሀኬት ።
ወዲያውም ቢጠይቅ ጊዜ ቃልቻው
ያ ኃይለ ሥላሴ አጥፊህ ነው አለው ።
አትስማሙምና ከጀኔራል ዊንጌት
በንጉሥ ተፈጥመህ ሀገር ልቀቅለት
ወዲያው ተሰደደ ከከተማ ወጣ
ጠላቱ በዝቶበት መድረሻ ስላጣ ።
ካፉፍ ላይ ሆነና እያንጐራጐረ
ወዳጆቹን ሁሉ እየተዘከረ
ያለፈውን ኑሮ ያነሣ ጀመረ
በአዲስ አበባ ላይ ድንቍርና ጐመን ዘርቼ ነበረ
በኮለጅ ማት ወርዶ መና ሁኖ ቀረ
ምንድር ማት ነው ብዬ በስላስለው
የጻድቃንም አይደል የኢየሱስ ማት ነው ።
ተበደልሁኝ ብዬ በቀርብ እቤቱታ
ንጉሥም ተጣሉኝ የመሬቱ ጌታ
ጐበዝ ሽማግሌ ጉብል ሕፃናት

ብጠይቅ ባስጠይቅ ሒጄ ጎረቤት
ላሽከራቸው ዕውቀት ባዋጅ በነጋሪት
ሰጥተውታል አሉኝ ይህን ሁላ መሬት ።
ንጉሡ ለጥበብ ሲረዱት አይቼ
እንዲያው ተሰደድሁኝ ርስት ጕልቴን ትቼ ።
እገዛው ነበረ ሰውን በውነቱ
እየለዋወጥሁኝ መልኬን በያይነቱ ።
አብሬያቸው ሳለሁ የሚያሞግሱኝ
ከተለየን ብለው ብዙ ስም ሰጡኝ ።
ስንፍና ብልግና መጥፎ ድንቊርና
እኛን እየገዛ ቀምበር ስላጠና
ኮሌጅ ገባንና ተሰልፈን በረድፍ
ብናሳየው ጊዜ መትረየስን መጽሐፍ
ዘሎ ገደል ገባ አልተገኘም በፉፍ
ንጉሥ ጭምር እንጂ መቼ ልጆች ብቻ
ከነሙሉ ተስማምተው ያረጉ ዘመቻ
ተኝታችሁ ዋሉ ዐርፋችሁ እደሩ
ብዬ ባስተማርሁኝ እንዲ ለማ አገሩ
መቸም አያውቅና የሰው ዘር ለክብሩ
ንጉሥ ተቈጥተው በኔ ላይ መከሩ
ታዘዘ ሊያጠፉኝ ተማሪያቸው ጠሩ
ወዲያው ተጫነብኝ ኮሌጅ መድፋቸው
የነጭ ጥይት ጕርሶ ሚዝገመገመው
የመትረየስ ጥይት መጽሐፍ መሣሪያቸው
ተሰጠ ለሁሉ ተማሪ አሽከራቸው
በየእጁ ያዘና ቢያርገበግባቸው
ዘመዶቼ ሁሉ ጠፉ መድረሻቸው
እየዞርሁ ባስጠይቅ ሰዎቹን በሙሉ
ጥይት አቀባዩ ያውም የሻምበሉ
የስንፍና ጠላት ሐይናስኪ ነው አሉ
የኔ ዘር ደመኛ ደጃዝማች ትጋት
ኀደኛው ነው አሉኝ በጦር ትምህርት ቤት
ደግሞም አቶ ርዳታ የቅናት ጠላት
አይለይም ከሱ ቀንና ሌሊት ።
ጥይቱ እንዳለቀ ወቴ ደቀ መዝሙር

ይቀበላል ቶሎ ያለምንም ችግር ።
የጥበብን አምላክ ቤተ መጻሕፍት
ይለዋል ፍጥረቱ አኀዜ ዓለማት
አንባቢ ሲጠይቅ ሁሉን ባንደበቱ
ካምላክ ቤተ መጽሐፍ ይሰማል ጸሎቱ ።
አማርኛ ግዕዝ ፈረንሳይ ጀርመን
እንግሊዝ ኢጣሊያ ጥንታዊው ላቲን
ሌሎቹም ቋንቋዎች ሚነበብባቸው
ቍጥራቸው ብዙ ነው እኛም አናውቃቸው ።
በዚህ ሁሉ ቋንቋ ፈጥኖ ሲመልስ
ለጠያቂው ሁሉ አለው የደስ ደስ ።
ቀኛዝማች ብልግና የጥንት አጋሚዶ
በመሳፍንት ጊዜ ሰውን መግዛት ለምዶ
አገሩን ሊሰልል ትላንትና ሂዶ
የጥበባት መጽሐፍ መድፉ ተቀይዶ
በኮሌጅ አዳራሽ ታላቁ ተራራ
ስላየው ጨነቀው በጣም ሆዱ ፈራ ።
ዱር ዱሩን ሩጦ ነፍሱን አወጣና
አመጣልኝ ለኔ ይህን ሁሉ ዜና ።
እኔና ስንፍና አለማወቅ ሁነን
ተሰደን ቀረን አገራችን ጥለን
ከምዕራብ የመጣ ጦር ኮሌጅ ቢወጋን
ከመሞት መሰንበት ይሻለኛል ብዬ
እሄዳለሁ ዱሩን ከተማዬን ጥዬ ።

ልብ ራስሽን ስላጣ ክፉ ክፉ ወሬ
ሲያወራ ሰማሁት አቶ ሀኬት ዛሬ
ስለተሸነፈ ገጥሞ ከራስሽ
ድል ሁኖ ማልቀሱን መጣሁ ልነግርሽ ።
ሳወራ ለራስሽ በረጅም አትቼ
ዘልዬ እንደሆነ እኔ ተሳስቼ ።
የማይሳሳት ሰው መቼም አይገኝ
አድርገሽ ይቅርታ አንቺ ንገሪኝ

ኢትዮጵያ የቀረም እንዳለ በል አራዳ እንውጣ
ሱቁን ከተማውን አሳይቼህ ልምጣ ።
ራሴ ሲጐትተን ጠጉሬ ሲያድግብኝ

ባዲስ ባዲስ መንገድ እሠራለሁኝ
የሚሠሩኝ ሰዎች ባዕዶቹ በሙሉ
በአፍ እየሰበኩ ገንዘቤን ሊበሉ
አዲስ ነው መንገዱ ታይቶም አያውቅ አሉ ።
አሮጌ እንዳይደለ ባውሮጳ አገር ሁሉ ።
ሌት ተቀን በልቤ እመኛለሁኝ
ያሁኑ ልጄ በእጁ እንዲሠራልኝ ።
እንዳይዝ ራሴ ቄሻሻ ኳኳት
በሰው አገር መንገድ ሳሙና አጠብሁት
ጥንታውያን ልጆቼ አሡስም ላሊበላ
ይሠሩልኝ ነበር ቤቶቼን በሞላ ።
እሠራለሁ ብሎ ገንዘቤን በከንቱ
ባዳ እንዳይበላብኝ በትንሽ ብልሐቱ
ተምሮ ሊሠራኝ የዛሬውም ልጅ
መሐንድስ ይማራል በሕንፃ ኮሌጅ ።
ጠቢብነትንም በተግባረ እድ
ራሱን እንዲችል የዛሬው ትውልድ
እነዚህ ከሌሉ የንግድ ትምህርት
ደግሞም ቍጭ ብሎ የቢሮ ጽሕፈት
አፋዊ ተረት ነው ፍሬም የለበት ።
ባላባት ነኝ ይበል በሥራውም ይኵራ
ራሴን ሊያስችለኝ በእጁ የሚሠራ ።
ዓለሙን የሚገርም ሕዝቡን ሚያስደንቅ
ተሠርቷል ለራሴ ልዩ ልዩ ሱቅ ።
ይህ ሁል የምታየው ከፒያሳ ሁነህ
የራሴ ነው እንጂ የማን መሰለህ ።
ደግሞም እልፍ ብትል ወዳዲስ ከተማ
ታያለህ ብዙ ቤት አቀዱ የተስማማ ።
ዝቅ ብለህም ብታይ ወደ ለገሐር
መንገድ ይመስላል የጣናን ባሕር ።
በምኒልክ ዘመን በኃይለ ሥላሴ
ብዙ ቤተ መንግሥት ሠራሁኝ ለራሴ ።
የምኒልክ ግቢ ገነተ ልዑል
በቅርብ የተሠራው አዲሱ ኢዮቤል
ሥራው ዕፁብ ድንቅ ነው በጣም ይገርማል ።

ብዙ መሥሪያ ቤቶች ሕዝብ ለማስተዳደር
አሉልኝ ለራሴ ምንም አልቸገር ።
ፍል ውኃ ዋኛለሁ ልታጠብ ራሴን
ሰውነቴ ይጽዳ ደስ ይበላት ነፍሴን
አንጎሌ እንዲረካ ልቤም እንዲስማማ
እሄዳለሁ ማታ ትያትር ሲኒማ ።

**ልብ** ሲኒማ ትያትር ያሠራሽውን
ንገሪኝ እናቴ ልወቀው ሁሉን ።

**ኢትዮጵያ** ሰውን ሚያስደስቱ በሐዲስ ሥራቸው
ከጠየቅሽኝማ ሚከተሉት ናቸው ።
ባገር ፍቅር ማኅበር ትልቁ አዳራሽ
ፀሐይ በመሰለው ሰው ገብቶ ሲያመሽ
አንጎሉን አድሶ ልቡናው ረክቶ
ይመለሳል ቤቱን ድካሙን ረሥቶ
ባለም የታወቀው ማዘጋጃ ቤት
ሁሉ ጊዜ ይሰጣል ለሰው ልጅ ሕይወት
በመኪና ሞላ ዐድዋ አደባባይ
መኳንንቱ መጣ ኃይለ ሥለሴን ሊያይ ።
ይህ ኃይለ ሥላሴ አሁን የተሠራው
በጣሙን ይገርማል ውስጡን ገብቶ ላየው ።
ያገራችን ውበት በሰፊው ደባይ
በጣም ያስደስታል ተሥሎ ሲታይ ።
ኢትዮጵያ ዐድዋ ደግሞም አምፒር
አንጎል ያድሳሉ የሰውን ልጅ ዘር ።
ከዚህ በላይ ካሉት ስሰማ ጭዋታ
የረፍቱ ጊዜዬ ያልፋል በደስታ ፡
አካሌ እንዲዳብር ኀይልም እንዳገኝ
ኳስ ምጫወትበት ብዙ ሜዳ አለኝ ።
ሚያስደስት በሥራው በሰፊ ሕንፃው
ሕገ መንግሥት አለኝ ዓለም ያወቀው ።
በሕንፃው በግንቡ በትጉህ ሥራው
በጣም ይገባኛል ባንኬን ላነሣው
ያለምንም ጉቦ ሰው ሳያስቸግሩ
ወጣቶች አሉበት ተግተው የሚሠሩ ።

**ልብ** የራስሽ ንብረቱ ብዙ ነው ዝርዝሩ

ስለዚህ እናቴ ነገርሽኝ ባጭሩ
ይህን ሁሉ ጥሪት የራስሽ ነው ለካ
እንጐሌ ደስ አለው ሰውነቴ ረካ ።
መወድስ ሰጥቼ ስለ ራስሽ ሀብት
እማዬ ለዛሬው እንሰናበት ።
ማሳሰብሽ አለኝ ደግሞም ከዚህ ሌላ
ነገ እንድታወጊኝ የአንጐልሽን በሞላ ።

<u>ኢትዮጵያ</u> የራሴን ያንጐሌን ደግሞም የልቤን
እነግርሃለሁኝ ብቻ ደኅና ሁን
ያልሽኝን መወድስ ለራሴ ነግረህ
ማልደህ እንድትመጣ ከቤትህ አድረህ
በል ደኅና ሁን ብዬ ሳሰናብትህ
አሳስብሃለሁ መሥራትን በጠና
ቀንና ሌሊቱን ሞት አይቀርምና ።

<u>ል ብ</u> ለራስሽ እንድቀኝ ከፈቀድሺልኝ
ይኸው መውድሱ እማዬ ስሚኝ ።

<u>መ ወ ድ ስ ።</u>

ሰውን ምታስደስት በጣም አዲስ አበባ
ሲያሸት ይታያል በሩቅ ቤተ መንግሥት ደቀ መዝሙር
ሊያወዳድር በጥበብ ሥነ ፍጥረቷን መንክር
ካሁስም ያደይ አበባ ወቍንን ደብረ ሳሊበላ ደንጐላም ጐንደር
ዐይነቷ ጥሩ ነውና
ከጥንት አበቦች ይልቅ ተክሎ አስቀመጣት በፍቅር
እኔምሂ ብጠይቅ ጊዜ አለቃ ታሪኩን መምህር
ሁሉን ያየዋልና በሰፊ ጊዜው መነጥር
ትበልጣለች አለኝ በጣም ከገዳም ከተማ በክብር
ምኒልክ የተከላት አዲስ አበባ ታላቅ ደብር ።

በድኅነት ምክንያት የደራሲው መጻሕፍት መታተማቸው ስለዘገየ የተዘረፈ መወድስ

ሥነ ጽሑፍ ወልድየ መከራው የበዛ
የይሁዳ ንጉሥ ተንኰል አበሻን ሲገዛ ተወልዶ
አገራችን መጠ ድንገት ከምዕራብ ክፍል ተሰዶ
ቀበረው አሉኝ ትላንትና ጃዱን ጠቅሎ ጣለና በቅንአት መንዶ
ሕዝብን በማወከ የታወቀው

ከጥንት ጀምሮ ተንኰል ከህን ያሳደገው አጋሚዶ ።
ድርሰትሂ ሰፊ አዝመራዬ በማሳ ድካም ነጕዶ
ረግፎ ቀር ለሰው ሳይሆን በመኪና በሬ ተኪዶ
በወርኀ ማኅተም መከር ከሰማይ መናፈግ ወርዶ
መቶታልና ለሰው እስኪ መስለው ድረስ ባዶ
ሰብልን ለማውደም የወረደው ድኅነት የጥፋት በረዶ

## ምዕራፍ ፱ ሸዋ (አንጐል)።

## መ ግ ለ ጫ

ከኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛቶች መካከል የሚገኝ የባዕድ ግዛት የማያዋስነው ሸዋ ነው። ያሁኑ ዘመን የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ አዲስ አበባ የሚገኘው በዚሁ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ ነው ። ሀገሩ ሜዳ ነው ፡ ረጃጅም ዛፍ ሣር ብዙ ወንዝ የለበትም ፤ በዳር በዳሩ ከመለግ የማይበልጡ ዱሮች አሉ ። በሜጫ አውራጃ መጠነኛ ጫካዎች ይገኛሉ ፡ ማን ኛቸውንም እኽል እንደ ቦታው ነው እንጂ ያበቅላል ። ግን አዝመራው የሚያፈራው በሰው ልፋትና ትጋት እንጂ በመሬቱ ስባት አይደለም ።

ሰው በጣም ታታሪ ነው ፡ የሚሠራውን ሁሉ የሚያደርገው በምክርና በትዕግሥት እንጂ በፍጥነት አይደለም ፡ አንጐልም የተባለበት ምክንያቱ ይህ ነው ፡ አውራጃዎቹ የሚከተሉት ናቸው ።

ሀ) መናገሻ ፤ ለ) ሰላሌ ፤ ሐ) ደብረ ብርሃን ፤ መ) ደብረ ሲና ፤ ሠ) ናዝሬት ረ) ጨቦና ጉራጌ ፤ ሰ) አምቦ ።

ወሰን ፡ በሰሜን ወሎና ጐጃም በምዕራብ ፡ ወለጋና ጅማ በደቡብ ፡ አሩሲ በም ሥራቅ ሐረርጌ ናቸው ።

ዓሣ ያላቸው ወንዞች ፤

አዋሽ ፡ ጅማ ፡ ጉደር ናቸው ። ትንንሽ ሐይቆች ፍል ውኃ ፡ መዋት በብዙ ይገኝበታል ።

አንጐልሽ ሸዋ ነው ምታስቢበት
ሌት ተቀን ይሠራል ያላንዳች ዕረፍት
በጆሮሽ ሰምተሽ በዓይንሽ ያየሽውን
አውጥተሽ አውርደሽ በልብሽ ያለውን
በአንጐልሽ አስበሽ አመጣሽ አልጋውን
በአንጐልሽ የሚኖር አልጋ ምሥጢርሽ
በቃልሽ ተነግሮ ሰው ዐወቀብሽ
ዐይንሽም አየና ይህንን ምሥጢር
ላንጐል መለሰለት ከዚያው እንዲኖር